# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE NINETEEN: «መጥፋት»

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of scenes:**

**SCENE ONE: ብሩክ AND ቅዱስ ON THE STREET IN LABORIA**

- **ብሩክ (M, 8)**
- **ቅዱስ (M, 8)**
- **አቶ ደንበል (M, 40)**

**SCENE TWO: ምህረት AND ዳንኤል MEET DURING BREAK**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE THREE: አቶ ጃለታ , MAMA ንጉሴ AND ንጉሴ AT HOME**

- **አቶ ጃለታ (M, 45)**
- **ወ/ሮ ዘውዲቱ (F, 35)**
- **ንጉሴ (M, 15)**

**SCENE FOUR: ምህረት MAKES HER WAY TO ዳንኤል 'S ROOM AFTER**

**CLASS**

- ምህረት (F, 15)

- ዳንኤል (M, 16)

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" የተሰኘው ድራማ 19 ኛ ክፍል ነው። የዛሬው ርዕስ «መጥፋት» ይሰኛል። ያለፈውን በትንሹ ለማስታወስ ያክል፤ የምህረት እና ዳንኤል የመጀመሪያ የፍቅር ቀጠሮ የት/ቤቱ ርዕሰ መምህርት ባደረጉት የተማሪዎች የመኝታ ክፍል ቁጥጥር ተስተጓጉሏል። ምህረት የሆነውን ሁሉ ለጓደኛዋ ትዕግስት አጫውታታለች። የርዕሰ መምህርቷ መምጣት ብቻ አልነበረም የምህረትን ስሜት የበጠበጠው፤

2. ምህረት (EPISODE 18, LINE 101): "አይ! ዳንኤል … ግን… ፈልጎ ነበር… እንዴት ብዬ ልንገርሽ?… ራሴን እንድሰጠው ፈልጎ ነበር። ግን እምቢ አልኩት።

3. ትዕግስት : "እምቢ አልሽው? እንደማትፈልጊ ነገር?"

4. ምህረት : "አዎ! እና አሁን በጣም ተናዶብኛል።

5. ትዕግስት (105): (…) "አይ ምህረት! (…)ብትቆይ አድገትሽን ታዘገያለሽ። ይህንን ታውቂያለሽ አይደል?

እናስ ምህረትበ አቋማ ትፀና ይሆን ወይንስ የጓደኛዋን ምክር? በሌላ በኩል ከምህረት ጋ የአንድ ክፍል ተማሪ የሆነው ንጉሴ የምህረትን ትኩረት ለመሳብ በሚል የወላጆቹን መኪና ሰርቆ ሲነዳ ሳይታሰብ ሰው ገጭቷል። ነገሮች ይበልጥ ተወሳሰበዋል።

6. **EPISODE 18, 43 SFX: LOUD EMERGENCY BRAKE**

7. **SFX: THUDDING SOUND**

8. ንጉሴ : " ሰው… ገጭቻለሁ መሰል። … ወይኔ!… ማንንም አላየሁም ነበር።

የምህረት ታናሽ ወንድሞች ብሩክ እና ቅዱስስ? ለነገሩ ወ/ሮ ለምለም ልጆቹን እኔ አሳድጋቸዋለሁ በሚል ወደ ላቦሪያ አምጥተዋቸው ነበር። ሆኖምአክስትየው በአደራ የተቀበሉትን ልጆች የማዕድን ማውጫ ባለቤት ለሆኑት ባለፀጋውየዳንኤል አባት አቶ ካሳሁን አስረክበው ለረጅም ሰዓታት እንዲሰሩ በመደረጋቸው ጠፍተው በሌላ ከተማ በርሃብ እና ብርድ እየተሰቃዩ ነው። ወደ ትውልድ መንደራቸው ለመመለስም መንገድ ላይ ገንዘብ እየለመኑ ነው። በእዚህ « መጥፋት » በተሰኘው 19ኛው ክፍል መልሰን እናገኛቸዋለን። ቅዱስ እና ብሩክ የሚቀመስ ነገር መግዣ ሳንቲም ለማግኘት እየለመኑ ነው።…

**SCENE ONE: ብሩክ AND ቅዱስ ON THE STREET IN LABORIA**

**9. SFX: RAINFALL POURING DOWN HEAVILY**

**KW BEGIN**

**10.** ቅዱስ: **(shivering from cold)** ብሩክ በስብሷል፤በእዛz ላይ በርዶኛል!

**11.** ብሩክ : **(also shivering)** አይዞክ ቅዱስ ። ዝናቡ አሁን ያቆማል። እንካ ይሀንን ካርቶን ያዝና ተሸፈን።

**12. SFX: CARDBOARD BOX BEING TORN APART**

**13.** ብሩክ : ትንሽ ሙቀት ይሰጥሀል። ቢያንስ ለአጭር ጊዜ። አዚህ ቆየኝ እዛች ጫፍ ላይ ልሂድ እና ትንሽ ገንዘብ ልለምን።

**14.** ቅዱስ: **(sad tone)** ወደ ቤት የምንሄድበት ለታክሲ ምን ያህል ገንዘብ ያስፈልገናል?

**15.** ብሩክ : ገና ብዙ ይቀረናል ቅዱስ ። ለዚህ ነው ልመናችንን መቀጠል ያለብን።

**16.** ቅዱስ : እንደዛማ ከሆነ ወደ አክስታችን ለምለም ቤት ብንሄድ ይሻላል።

**17.** ብሩክ : አይሆንም። እሷ ናት ፍዳችንን እንድናይ ወደ ማዕድኑ ስራ የላከችን። ምንም አትረዳንም፤ ረድታንም አታውቅም። እሷ ጋር ነገሮች በሙሉ ይባባሳሉ ቅዱስ። እዚህ ጠብኝ ። መጣሁ።

**KW END**

**18. SFX: FOOTSTEPS WALKING AWAY**

**19. SFX: THUNDERSTORM AND MORE RAIN**

**20.** ብሩክ : **(goes back to begging)** እርዱን እባካችሁ። ወደ ቤታችን የምንመለስበት ገንዘብ ስጡን።

**21. SFX: COINS JINGLING IN A CAN**

**22.** አቶ ደንበል : ይኼውልህ የኔ ልጅ **(throws a coin in the can)**

**23. SFX: COIN LANDING IN THE CAN**

**24.** አቶ ደንበል : እዚህ መንገድ ላይ መሆን የለብህም። አየሩ ቀዝቃዛ ነው። ትታመማለህ። አቤትህ የት ነው ልጄ?

**25.** ብሩክ : በጣም ሩ ሩ ሩ ቅ ነው። ታንዲካ ይባላል። የት እንደሆነ ያውቁታል?

**26.** አቶ ደንበል : **(shocked)** በእውነት? ታንዲካ? ከዚህ በጣም ሩቅ እኮ ነው ፤ ሌላ ሀገር ነው። ለመሆኑ ስምህ ማነው?

**27.** ብሩክ : ብሩክ

**28.** አቶ ደንበል : እሺ ብሩክ ! እኔ ደግሞ ደንበል እባላለሁ። እዚህ እንዴት እንደመጣህ ንገረኝ። ወላጆችህ የት ናቸው?

**SILENCE**

**29.** አቶ ደንበል : አይዞህ አትፍራ! ልረዳህ ብዬ ነው። ...

**30.** ብሩክ : እኛ ወደቤታችን መመለስ ብቻ ነው የምንፈልገው። **(starts to cry)**

**31.** አቶ ደንበል : እኛ ስትል ስንት ናችሁ? ከአንተ በስተቀር ሌላ ሰው አጠገብህ አይታየኝም።

**32.** ብሩክ : መንታ ወንድሜ ቅዱስ አብሮኝ አለ። እዛጋ ከካርቶኑ ስር ነው።

**33.** አቶ ደንበል : ወይጉድ እናንተ ምስኪኖች።

**34.** ብሩክ : ሊረዱን ይችላሉ?

**35.** አቶ ደንበል : እ... ምናልባት እችላለሁ...የከባድ መኪና ሹፌር ነኝ። ታዲንካም መንገዴ ላይ ነው። ግን መጀመሪያ እንዴት እንደመጣችሁ ንገረኝ። ኋላ ችግር እንዲገጥመኝ አልፈልግም።

**36.** ብሩክ : አክስታችን ወ/ሮ ለምለም ትባላለች። እሷ ነች ያመጣችን።

**37.** አቶ ደንበል : እና አክስታችሁ ወ/ሮ ለምለም የት ነው አሁን ያሉት?

**38.** ብሩክ : አላውቅም። ለረጅም ጊዜ አላየኋትም። ግን እባክዎን ወደ እርሷ መሄድ አንፈልግም።

**39.** አቶ ደንበል : ተረጋጋ አይዞህ። ስለዚህ ከአክስታችሁ ወ/ሮ ለምለም አምልጣችሁ ነው። ልክ ነኝ?

**SILENCE**

**40.** ብሩክ : **(crying desperately)** እንደገና ወደ ማዕድን ማውጫው መመለስ አንፈልግም። እዛ ከሄድን ይመቱናል። ወደ ወላጆቻችን ጋ ነው መሄድ የምንፈልገው።

41. አቶ ደንበል : (understands what’s going on) ማልቀስህን አቁም ልጄ። አይዞህ። መኪናዬን ይዤ እዚህ የደረስኩት ዛሬ ጠዋት ነው። ለሚቀጥሉት ሁለት ቀናት እዚህ እቆያለሁ። እናም እቃዬን አሰባስቤ ስጨርስ ኪሲምባ ድረስ እወስዳችኋለሁ። እንጂማ በዚህ ሁኔታ አይቻችሁ ጥያችሁ አልሄድም።

42. ብሩክ : (with confidence) ቅዱስ እና ብሩክ እንጠብቅዎታለን።

43. አቶ ደንበል : ጥሩ። በል ለሁኑ እንካ ይሄውልህ። ትንሽ ገንዘብ ናት። …

44. **SFX: COINS HANDED OVER**

45. አቶ ደንበል : …ግን ለአንተ እና ለወንድምህ ምግብ ሊገዛላችሁ ይችላል። በቀሪው ገንዘብ ደግሞ ሞቅ የሚያደርግ ብርድ ልብስ ግዙበት። እና--

46. ብሩክ: (cuts him short in joy) አመሰግናለሁ። በጣም ነው የምናመሰግነው። (calls out in extreme joy) ቅዱስ! ቅዱስ!

47. አቶ ደንበል : ስማኝ ቆይ ልንገርህ። ….መኪናዬ የት እንደቆመ አሳይሀለሁ። ዛሬ ሌሊት እዛ ማደር ትችላላችሁ።

48. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE TWO: ምህረት , እና ዳንኤል MEET DURING BREAK</u>**

49. **SFX: BELL RINGING FOLLOWED BY STUDENTS CHATTING DURING BREAK**

50. **SFX: STEPS ምህረት COMES OVER TO ዳንኤል 'S DESK**

51. ምህረት : ዳንኤል እንዴ ላናግርህ እችላለሁ?

**KW BEGIN**

52. ዳንኤል: (indifferent)እሺ. ምህረት ታድያስ?

53. ምህረት : በእውነት ምን ማለትና ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም። ግራ ተጋብቻለሁ።

54. ዳንኤል : እና ምን እንድልሽ ትፈልጊያለሽ? የምትፈልጊውን ስታውቂ ብንነጋገር ይሻላል።

55. ምህረት : አባክህ ዳንኤል ።

**KW END**

56. ዳንኤል: (sighs) ምን ላርግሽ ምህረት ?

57. ምህረት : ዳንኤል ምን መሰለህ። በሁለታችን መካከል ነገሮች አስቸጋሪ እንደሆኑ ይገባኛል። ግን እኔ አሁን ከባድ ችግር ውስጥ ነኝ። እና በአሁን ሰዓት አንተ ብቻ ትመስለኛለህ ችግሬን ሊያቃልልልኝ የሚችል።

58. ዳንኤል: (interested) ምንድን ነው? እንዴት ነው ልረዳሽ የምችለው?

59. ምህረት : አንተን መጠየቅ ስላለብኝ በጣም አዝናለሁ … ግን አባቴ ለዚህ ሳምንት የሚሆን ለምሳዬ እና ለታክሲ የሚሆን ገንዘብ ሊሰጠኝ አልቻለም። ትዕግስትን እንዳልጠይቃት እሷ ባለፈው ጊዜ ሰጥታኝ ነበር።

60. ዳንኤል : ምህረት በእኔ ሁልጊዜ ልትተማመኚ ትችያለሽ። ከክፍል ስንወጣ የተወሰነ ገንዘብ እሰጥሻለሁ። ሌላ የምረዳሽ ነገር አለ?

61. ምህረት : የለም ይኼው ነው።

62. ዳንኤል : ጥሩ እንግዲያውስ ቻው።

63. **SFX: CHAIR BEING PUSHED BACK**

64. ዳንኤል: (calls out) ትዕግስት! ትዕግስት! ቆይኝ አንዴ?…

65. ምህረት: (jealously) ዳንኤል ትዕግስትን ለምን ፈለካት?

66. ዳንኤል: (indifferent) ምን? ከሌሎች ተማሪዎች ጋ እንዳልነጋገር ልትከለክይኝ ነው እንዴ?

67. ምህረት: (getting angry) ግን ለምን ትዕግስትን ጠራሃት? እሷኮ… (swallows hard) ጓደኛዬ ናት ዳንኤል ።

68. ዳንኤል : እና? ያንቺ ጓደኛ የሆነች እንደሆነ የኔም ጓደኛ ልትሆን አትችልም እንዴ?

69. ምህረት : አይ እንደዛ ማለቴ ሳይሆን! … ሁለታችሁ የምትደባበሩ ይመስለኝ ነበር። ለዛ ነው ትንሽ ግራ የተጋባሁት።

70. MUSIC INTERLUDE

<u>SCENE THREE: አቶ ጃለታ , WIFE AND ንጉሴ AT HOME</u>

71. SFX: SOMEONE BEING SLAPPED

72. ንጉሴ : (cries in pain) አሀሀ!

73. ወ/ሮ ዘውዲቱ : (screaming) ጃለታ፤ ይበቃል ።በቃ ተወው እንጂ ።እንዲህ በጥፊ ብትጠፈጥፈው የምትቀይረው ነገር የለም።

74. አቶ ጃለታ: (furiously) ምን አባህ ስታስብ ነው? እእእ ንጉሴ !! ሴትየዋን እኮ ልትገድላት ትችል ነበር። ምን እንደሰራህ ለመሆኑ ታውቃለህ?

75. ወ/ሮ ዘውዲቱ : ያውቃል። ያውቃል! ንጉሴ በል አባትህን ይቅርታ ጠይቅ። ጃለታ ተወው ይሂድ። የእስካሁኑ ይበቃዋል።

76. አቶ ጃለታ: (authoritative) ንጉሴ ፤ አሁን ወደ ክፍልህ ግባ እና አስብበት። ስለሰራኸው ስህተት በደንብ አስብበት። እስከምጠራህ ድረስ ከክፍልህ እንዳትወጣ። ግልፅ ነው?

77. ንጉሴ : (grumbling quietly) እእእምም

78. አቶ ጃለታ : ምን ድን ነው የምታልጎመጉመው? እሺ ስትል ነው የሰማሁት?

79. ንጉሴ : (quietly) አዎዎን

80. SFX: FOOTSTEPS WALKING AWAY

81. SFX: DOOR OPENING AND CLOSING

82. አቶ ጃለታ : ይሄን ልጅ እያበላሸሽው ነው። በቃ እኮ እንደው አልምጥ ሆኖ ቀረ።

83. ወ/ሮ ዘውዲቱ: (defensive) እና መቼም አሁን ሁሉም ስህተት የኔ ነው ልትል ነው አይደል? ለሁሉም ነገር ተጠያቂዋ ፣ ተወቃሽዋ አንቺ ነሽ ልትል ነው?

84. አቶ ጃለታ: ዘውትር ለንጉሴ ጠበቅነት ትቆሚያለሽ። ልክ እንደ ስድስት አመት ልጅ ነው የምታይው። ያመጣብንን ጉድ በሙሉ ተመልከች። እስካሁን ማን እንደዘረፈን ገና አላወቅንም። አሁን ደግሞ ይሄ ጎዶሎ ሌላ ጣጣ ይዞ መጣ። (takes deep breath) ይሄን ልጅ እንደው ምን አባቴ ላድርገው?

85. ወ/ሮ ዘውዲቱ : ለፖሊሱ ጉቦ ሰጥተናል ጃለታ - አለቀ! ንጉሴን አሁን ለቀቅ አርገው። ይህን ማሰላሰሉን ትቶ ይልቁንስ ትምህርቱ ላይ ትኩረት ይስጥ።

86. አቶ ጃለታ : አንቺማ ምን አለብሽ። ጉዳዩ ያበቃ መሰለሽ? የተገጨችውን ሴትዮ አስበሻታል? እስካሁን ድረስ እኮ ሆስፒታል ነው ያለችው። እእእ?

87. MUSIC INTERLUDE

__SCENE FOUR: ምህረት MAKES HER WAY TO ዳንኤል ’S ROOM AFTER CLASS__

88. SCHOOL YARD ATMO

89. **SFX: ምህረት STRUGGLING TO GET THROUGH A THICK BUSH**

90. ምህረት: **(straining)** ወይኔ ጉዴ ምን እያረኩ ነው? ምህረት አዕምሮ የለሽም እንዴ?ያለፊው ሳያንስ እንደገና ተደብቆ ዳንኤል ክፍል መግባት—ሳላብድ አልቀረሁም። ...

91. **SFX: DRESS RIPS**

92. ምህረት : **(startled)** ኤጭ ምን አይነት ነገር ነው። የሽቦ አጥሩ የትምህርት ቤት ዮኒፎርሜን ቀደደው። ሲያናድድ።

93. **SFX: SLOW FOOTSTEPS ON EARTH**

94. ምህረት : ኡፍ። በስተመጨረሻ የወንዶቹ ግቢ ገባሁ። ... የዳንኤልን በር ሳንኳኳ ፊቱን እስካይ ቸኩያለሁ **(takes deep breath)** ቀሚሴ ተቀደደ እንጂ ሌላውስ ከባድ አልነበረም።

95. **SCHOOL COMPOUND ATMO FADE OUT**

96. **DORMITORY ATMO**

97. **SFX: GENTLE KNOCKING ON DOOR, HEARD FROM INSIDE**

98. ዳንኤል : ማነው? ግባ በሩ ክፍት ነው።

99. **SFX: DOOR OPENS SLOWLY**

100. ምህረት : ታድያስ ዳኒ ?

101. ዳንኤል : ምህረት ? በህልሜ ነው በውኔ?

102. **SFX: DOOR BEING OPENED AND CLOSED**

103. ዳንኤል : በፍፁም አልጠበቅኩሽም። ምንድን ነው ነገሩ ምህረት ? ገንዘቡን በኋላ እሰጥሻለሁ ብዬ ነበር … ለሱ ደግሞ እዚህ ድረስ መምጣት አስፈላጊ አልነበረም …

104. ምህረት: (shyly) ዳንኤል … ስለጠየከኝ ነገር….እያሰብኩበት ነበር።

105. ዳንኤል : እሺ እና…መልስሽ ምንድን ነው?

106. ምህረት : መልሴን ከመናገሬ በፊት አንድ ነገር ቃል ግባልኝ።

107. ዳንኤል : (anxiously) እሺ, ግን በቅድሚያ አንዴ ልነሳ

108. SFX: STANDING UP FROM BED

109. ዳንኤል : ውይ ምህረት የትምህርት ቤት ልብስሽ ምን --

110. ምህረት : (cuts him short) ከኔ ሌላ፤ ሌላ ልጅ ጋ እንደማትሄድ ቃል ግባልኝ።

111. ዳንኤል : (impulsively) በፍፁም። ቃል እገባልሻለሁ።

112. ምህረት : በዕረፍት ጊዜም  ከትዕግስት ጋ ሆነህ አታወራም።

113. ዳንኤል: (laughs) ኖ! ትዕግስት ለራሷ እንዴት እንደምትደብረኝ ብታውቂ።

114. ምህረት : (chuckles) ልትጠላት እንኳን አያስፈልግም(short pause) ለአንተ አሁን ክብረ ንፅህናዬን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ።

115. MUSIC INTERLUDE

## 116. OUTRO - NARRATOR:

ይገርማል። ምህረት በርግጥ ሀሳቧን ቀይራለች።…እኛም በጊዜ የመኝታ ክፍሉን ለቀን ብንሄድ እና የ19ኛውን ክፍል እዚህ ላይ ብናጠቃልል ይሻላል። «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» ስለሚሰኘው ድራማ የበለጠ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ድረ ገፅችንdw.de/lbeን ጎብኙ። እዛ ላይ ዳንኤል ለጓደኞቹ ያዘጋጀውን የቪድዮ ዘገባም ታገኛላችሁ። ዳንኤል ለጓደኞቹ ምን ሊነግራቸው እንዳሰበ ገምቱ። …በተጨማሪ በፌስቡክ አድራሻችን ላይም እንዲሁ መከታተል ይቻላል። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ፤ ደህና ሁኑ።